

: amharisk

Informasjon til asylsøkere i Norge

NOAS

# በኖርወይ

## የጥገኝነት ከለላ ለሚጠይቁ ሰዎች የተዘጋጀ መመርያ፣

ይህ የመረጃ ጥራዝ የተዘጋጀው በኖርወይ NOAS ተብሎ በሚጠራ ለጥገኝነትና ከለላ ምክር የሚለግስ ድርጅት ነ።
NOAS መንግሥታዊ ያልሆነ የሰብአዊ መብት ድርጅት ሲሆን፣ሥራውም መረጃንና የህግ እርዳታን ጥገኝነትና ከለላን ለሚጠይቁ ሰዎች መስጠት ነው።

እንዲረዳ ሆኖ የተቋቋመ ድርጅት ነው። ይህ ጥራዝ ለእርስዎ በኖርወይ ውስጥ ጥገኝነትንና ከለላን ለሚፈልጉ ሰው ጠቃሚ መረጃዎችን እንዲያካትት ተደርጎ የተዘጋጀ ነው።

**በዚህ ጥራዝ ውስጥ ከዚህ በታች ስለተዘረዘሩት ጉዳዮች ሊያነቡ ይችላሉ፡-**

- የጥገኝነት ከለላ መብት ሊኖረው የሚችለው ሰው ማነው?
- በሰብአዊነት መርህ መሰረት የመኖሪያ ፈቃድ ሊሰጠው የሚችለው ማን ነው?
- የጥገኝነት ከለላ ማመልከቻዎትን የሚያስተናግደው አገር የትኛው ነው?
- በኖርወይ ውስጥ የጥገኝነት ከለላ ጥያቄዎትን የሚያስተናግደው ማነው?
- የጥገኝነት ከለላ ባቀረቡበት ወቅት ምን ሊከሰት ይችላል?
- በጥገኝነት ከለላ ዙርያ ቃለ-መጠይቅ በሚደርግልዎ ጊዜ ሊያውቁት የሚገባ አስፈላጊ ምክር
- እንደጥገኝነትና ከለላ ጠያቂነትው ሊኖርዎት የሚችለው መብትና ግዴታው
- ሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ

## 1. የጥገኝነት ከለላ መብት ሊኖረው የሚችለው ሰው ማነው?

ለግድያ፥ለአሰቃቂ ግርፋትና ሰቆቃ፥ ወይም ለሌላ አጅግ አስከፊ ሰቆቃዊ ጥቃቶች የተጋለጡና ወደ ትውልድ አገርዎ ቢመለሱ ለነኝህ ጥቃቶች የበለጠ የሚጋለጡ ሰው ሆነው ከተገኙ፣ የጥገኝነት ከለላ የማግኘት መብትዎ የተከበረ ነው። ነገር ግን በትውልድ አገርዎ ያለው መንግሥት የርስዎን ደህንነትና ከለላ የሚጠብቅልዎት ከሆነ በኖርወይ የጥገኝነት ከለላ የማግኘት መብት የለዎትም።

በዓለም አቀፍ ህግ ድንጋጌ ስምምነት መሠረት፣ ማነው የጥገኝነት ከለላ የሚያስፈልገው በሚለው ላይ ኖርወይ ልትከተላቸው የምትገደድባቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች በህግ ተቀምጠዋል።

## 2. በሰብአዊነት መርህ መሰረት የመኖርያ ፈቃድ ሊሰጠው የሚችለው ማነው?

የጥገኝነት ከለላ የመጠየቅ መብት ከሌለዎ፣ መንግሥት ለመኖርያ ፈቃድ ማግኛ ናቸው ብሎ ያስቀመጣቸውን መስፈርቶች ማለትም ጥብቅ የሆነ የሰብአዊ መብት ግንዛቤ፣ ወይም ከኖርወይ ጋር ያለዎትን ልዩ ትሥሥር ገምግሞ የመኖርያ ፈቃድ ሊያገኙ ይችላሉ። ይህም በሰብአዊ ርህራሄ መሰረት ድንጋጌ ላይ የተመረኮዘ የመኖሪያ ፈቃድ ተብሎ ይታወቃል።

እንደ ህጉ ከሆነ፣ ይህን የመኖርያ ፍቃድ ለማግኘት ፓስፖርት እንዲኖርዎ ያስፈልጋል። ለመንግሥት ፓስፖርትዎን ካላቀረቡ የመኖርያ ፈቃድ ጥያቄዎ በመንግስት ውድቅ ሊደረግ ይችላል ወይም የተገደበ ፈቃድ ሆኖ ቋሚ የመኖርያ ፈቃድን መብት የሚነፍግና ቤተሰብዎም ከርሶ ጋር እንዳይቀላቀል የሚያግድ ነው።

## 3. የጥገኝነት ከለላ ማመልከቻዎትን የሚያስተናግደው አገር የትኛው ነው?

በኖርወይ የጥገኝነት ከለላ የጠየቀ ሰው ሁሉ ማመልከቻው በኖርወይ ይታይለታል ማለት አይደለም። የደብሊን የጋርዮሽ የጋራ ስምምነቶች  ማለት በአውሮፓውያን አገሮች መካከል አብሮ በመተባበርና አብሮ በመሥራት ጥገኝነትና ከለላ ጠያቂው ሰው ጉዳዩ ባንዱ የደብሊን አገራት ብቻ እንዲታይለት የሚያደርግ ስምምነት ነው።

የጥገኝነት ከለላ ማመልከቻዎ በዳብሊን አገራት አብሮ የመሥራት ስምምነት ውስጥ ከተካተቱት በአንደኛው ሀገር ውስጥ ሊታይ የሚችለው፣ በዚያ ሀገር ውስጥ፡-

- የጣት አሻራዎ የተመዘገበ ከሆነ፣
- ጥገኝነት ጠይቀው ከሆነ፣
- ቪዛ ወይም የመኖሪያ ፈቃድ ካለዎት፣
- የቅርብ  ቤተዘመድ ካለዎት፣

የኖርወይይ መንግስት ጉዳዩን መርምረው ወደሌላ ሀገር መተላለፍ ያለብዎት መሆኑን ለመወሰን ከሁለት እስከ ስድስት ወራት ጊዜ ሊወስድባቸው ይችላል።

ተጨማሪ መረጃ የሚፈልጉ ከሆነ፣ ከNOAS ስለ ዳብሊን የጋራ ስምምነት በራሪ ጥራዝ ሊያገኙ ይችላሉ።

## 4. በኖርወይ ውስጥ የጥገኝነት ከለላ ጥያቄዎትን የሚያስተናግደው ማነው?

የስደተኞች ጉዳይን የሚመለከተው ባለስልጣን /UDI/ የኖርወይ መንግስት አካል ነው። የዳይሬክቶሬቱ ሠራተኞች ቃለ-መጠይቅ ያደርጉልዎታል። የመኖሪያ ፈቃድ የሚሰጥዎት ወይም የማይሰጥዎት ስለመሆኑም ይወስናሉ። UDI ሁሉንም የጥገኝነት ማመልከቻዎች በጥንቃቄ ይገመግማል፣ እያንዳንዱንም ማመልከቻ በግል ያስተናግዳል።



## 5. የጥገኝነት ከለላ ባቀረቡበት ወቅት ምን ሊከሰት ይችላል?

**ጥገኝነትና ከለላ ጠያቂ ሆነው ከፖሊስ ዘንድ ሲመዘገቡ፣**

ፖሊስ ፎቶግራፍ ያነሳል፣ የጣት አሻራዎትንም ይወስዳል። ስለማንነትዎ፣ ወደ ኖርወይም አመጣጥዎ በየት በኩል እንደነበረ ይጠይቅዎታል። በተጨማሪም እርስዎ ለምን የጥገኝነት ከለላ ጥያቄ እንዳቀረቡ ኡደኢ/UDI ይጠይቅዎታል። ስለማንነተዎ የሚገልጹ መታወቂያ ወረቀቶች ካለዎት በምዝገባ ወቅት ማቅረብ አለብዎት።

**ወደ ስደተኛ መጠለያ ማዕከል ይተላለፋሉ**

ከምዝገባ በኋላ ወደ ስደተኛ መጠለያ ማእከል ይወሰዳሉ። ለጥቂት ቀናት ከዚያ ቆይታ ካደረጉ በኋላ ወደ አንድ ሌላ ጊዜያዊ መጠለያ ማዕከል ወይም ወደ አንድ መደበኛ መጠለያ ማዕከል ይመደባሉ።  በማእከሉ ውስጥ ባሉ ሰራተኞች አማካኝነት ስለ መብትና ግዴታዎ ተጨማሪ መረጃ ይሰጥዎታል።

**የሳንባ ነቀርሳ ምርመራ ይደረግልዎታል**

በእንግዳ መቀበያው ማዕከል መስተንግዶ በተደረገልዎት በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ቀናቶች ውስጥ፣ የሳንባ ነቀርሳ ምርመራ ይደረግልዎታል። ይህ ለሁሉም ሰው ግዴታ ነው። ስር የሰደደ ደዌና አስቸኳይ ክትትል የሚያስፈልገው ህመም ካለብዎ ለጤና ቢሮው ያሳውቁ።

**ከ NOAS መረጃ እና መምሪያ ይሰጥዎታል**

በእንግዳ መቀበያው ማዕከል የአቀባበል መስተንግዶ በተደረገልዎት በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ቀናቶች ውስጥ ከNOAS መረጃ ይሰጥዎታል። NOAS መንግሥታዊ ያልሆነ በሰብአዊነት መርሆ ላይ የተመሰረተ በኖርወይ የጥገኝነት ከለላ ለሚጠይቁ ሰዎች መብት የሚሠራ ድርጅት ነው ። በእንግዳ መቀበያው ማዕከል የNOAS ዋና ሚና ለጥገኝነትና ከለላ ጠያቂው ሰው መረጃንና መምርያ መስጠት ነው። በማዕከሉ ውስጥ የጥገኝነት ጥያቄ የሂደት አሰራሮችን በተመለከተ የመረጃ ፊልም እንዲመለከቱ ይደረግና ከአንድ የNOAS ሠራተኛ ጋር እንዲነጋገሩ ይደረጋል። የንግግሩ ዋና አስፈላጊነት በቀጣይነት ከUDI ጋር ለሚያደርጉት ቃለ-መጠይቅ ዝግጅት እንዲያደርጉ ለማገዝ ነው። ይህ ውይይት በጥገኝነት ከለላ ዙርያ ሊኖርዎት ስለሚችለው ጥያቄ መልስ ለማግኘት ይረዳዎታል። ውይይቱ የሚደረገው እርስዎ በአግባቡ በሚረዱት ቋንቋ ነው።



በዳብሊን ህግ ድንጋጌ ስምምነት መሠረት ወደ አንድ ሌላ የአውሮፓ አገር ሊተላለፉ የሚችሉ ከሆነ ለዚህ የሚሆን ትክክለኛ መረጃ እንዲያገኙ፣ ይህንንም ለNOAS መግለጽ አስፈላጊ ነው:: የNOAS ሠራተኞች ሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው::

### በUDI ቃለ-መጠይቅ ይደረግልዎታል

የጥገኝነት ከለላን በተመለከተ የሚቀርብልዎ ቃለ-መጠይቅ ለምን የጥገኝነት ከለላን እንደፈለጉ ለማስረዳት የሚያስችልዎት ምቹ ሁኔታ ነው:: እንደተለመደው ከሆነ የጥገኝነት ከለላን በተመለከተ የሚደረገው ቃለ-መጠይቅ በርካታ ሰዓታትን ይወስዳል:: ወደ ትውልድ አገርዎ ቢመለሱ በተጨባጭና በዝርዝር ምን እንደደርሰብዎት፣ ወደ አገርዎ ቢመለሱም ምን እንደሚፈሩና ሊደርስብዎት የሚችለውን ነገር ሁሉ መናገር አለብዎት:: በቃለ-መጠይቁ ወቅት አንድ አስተርጓሚ በቦታው ይቀርብልዎታል:: አስተርጓሚው ሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ እና ገለልተኛ መሆን አለበት:: እንዲሁም ወገን ያልያዘ መሆን አለበት::  እየተባለ ስላለው ነገር ማናቸውንም ያልተረዷቸው ነገሮች ካሉ ወዲያውኑ ለቃለ-መጠይቅ አድራጊው መንገር ይገባል::

የጥገኝነት ከለላው ቃለ-መጠይቅ በሚያበቃበት ወቅት በቃለ-መጠይቁ ወቅት ስላስመዘገቡት ቃልዎ ማረጋገጫ ፊርማዎትን ያሰፍራሉ:: ይህ ከመሆኑ በፊት አስተርጓሚው የተጻፈውን በንባባ ያሰማዎታል:: በሪፖርቱ ውስጥ የተካተቱን ያልተስማሙባቸውን ሃረጋት መለውጥ ካስፈለገዎት ፊርማዎትን ከማስቀመጥዎ በፊት መናገር መቻል አለብዎት::

### ከUDI መልስ በሚጠብቁበት ወቅት ወደሚኖሩበት ወደ አንድ መደበኛ የመቀበያ ማዕከል ይዘዋወራሉ ፣

መጠለያ ማዕከሉ በነጻ የሚኖሩበት ስፍራ ነው:: ከ UDI መልስ እየጠበቁ ባለበት ወቅት ከፈለጉ በግልዎት መኖር ይችላሉ፣ ነገር ግን በዚህ ወቅት ምንም የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት አይችሉም:: መኖሪያ ስፍራዎትን ከቀየሩ ለመጠለያ ማዕከሉ አዲሱን አድራሻ ማሳወቅ ይኖርብዎታል፤ እነሱ ደግሞ የእርስዎን አዲሱን አድራሻ ይመዘግባሉ። አድራሻዎ መመዝገቡ ከUDI ለሚላክልዎት መልስ በአድራሻዎ እንዲደርስዎ የሚያስችል በመሆኑ አስፈላጊ ነው::

### አዲስ መረጃ

ከጥገኝነት ቃለ-መጠይቁ በኋላ ለእርስዎ የጥገኝነት ማመልከቻ አስፈላጊ የሆነ አዲስ መረጃ ካገኙ፣ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ወዲያውኑ ለUDI ማሳወቅ አለብዎት። ይህንን መረጃ ቀደም ሲል ያልጠቀሱት ለምን እንደሆነም መግለጽ አለብዎት። የመጠለያ ማዕከሉ ሠራተኞች ምን ማድረግ እንደሚገባዎ ሊገልጽልዎት ይችላሉ።

### ከUDI መልስ እስኪላክልዎት ይጠብቃሉ

UDI የእርስዎን የጥገኝነት ማመልከቻ አይቶ ለመጨረስ ከጥቂት ሳምንታት ጀምሮ እስከ አንድ አመትና ከዚያ በላይ ጊዜ ሊወስድበት ይችላል። ጉዳዩ ረጅም ጊዜ ከወሰደ ይህ ሊሆን የሚችለው እርስዎ የሰጡት መረጃ ትክክል ስለመሆኑ UDI ምርመራ ማድረግ ስለሚገባው ሊሆን ይችላል። ከዚህ በተጨማሪም UDI በእርስዎ የትውልድ አገር ውስጥ ስላለው ሁኔታ ምርመራ እያደረገ ስላለና ወይም ሌሎች በርካታ ሰዎች ከ UDI መልስ እየጠበቁ ስለሚገኙ ሊሆን ይችላል።

## ከUDI መልስ ይሰጥዎታል፡ የመኖሪያ ፈቃድ ይሰጥዎታል ወይም ኣሉታዊ መልስ ያገኛሉ፣

### የመኖሪያ ፈቃድ

የመኖሪያ ፍቃድ ከተሰጥዎ የመኖርያ ስፍራ አጥቢያ ወይም ኮምዩነ እንዲሰጥዎ ይደረጋል። ይህንንም ጉዳይ በተመለከተ በመጠለያ ማዕከሉ ተጨማሪ መረጃ ያገኛሉ።.

### አሉታዊ መልስ ማግኘት

ያቀረቡት የጥገኝነት ከለላ ማመልከቻ አሉታዊ መልስ ካገኘ ይግባኝ የማለት መብትዎ የተጠበቀ ነው። ብዙ ጊዜ ይግባኝ ለማለት እንዲረዳዎ ለአምስት ሰአታት ያህል መንግሥት የሚከፍለው ነጻ ጠበቃ ማግኘት ይችላሉ። ይግባኝዎትን በሶስት ሳምንታት ውስጥ ማቅረብ አለብዎት። በኖርወይ ውስጥ መኖር የሚፈቀድልዎ ይግባኝዎ እየታየ እስካለበት ጊዜ ድረስ ብቻ ነው። ነገር ግን ማመልከቻዎ በግልጽ መሠረት የለሽ መሆኑን UDI ካመነበት መቆየት አይችሉም።

### የኖርወይ የስደተኞች ይግባኝ ቦርድ UNE

ይግባኝዎትን የሚመረምረው UNE ወይም ይግባኝ ቦርዱ ነው። UNE ስብሰባ ሊጠራዎት ወይም ተጨማሪ መረጃ እንዲያቀርቡ ሊጠይቅዎ ይችላል።

### ጥያቄዎ ኣሉታዊ መልስ ካገኘ ወደ ትውልድ አገርዎ የመመለስ ግዴታ አለብዎት።

ፖሊስ ባስቀመጠልዎ የጊዜ ገደብ መሠረት ወደ አገርዎ መመለስ አለብዎት። አብዛኛውን ጊዜ በሁለት ሳምንታት ውስጥ ሲሆን፣ ይህ የጊዜ ገደብ ካለፈ ኖርወይ ውስጥ ለመኖር ሕጋዊ መብት አይኖርዎትም።
ጥያቄዎ እስከመጨረሻው ውድቅ ከተደረገ ማለትም UNE የUDIን የጥገኝነት ከለላን ያለመስጠት ውሣኔ ካፀናው በበጎ ፈቃደኝነት በዓለም አቀፍ የስደተኞች ጉዳዮች ድርጅት (IOM) በኩል ለመመለስ መምረጥ ይችላሉ፣ አለዚያም በፖሊስ ተይዘው ከአገሪቱ እንዲወጡ ይደረጋል። ይህም ተገዶ መመለስ ይባላል።

### በፍቃደኝነት ወደ ትውልድ ኣገርዎ መመለስ፣

የኖርወይ መንግሥት በፈቃደኝነት ወደ ትውልድ አገርዎ እንዲመለሱ ሁኔታዎችን ያመቻችልዎታል። በፈቃደኝነት መመለስ ማለት በፈቃደኝነት ድጋፍ ኣግኝቶ የመመለስ ፕሮግራም ተብሎ በሚጠራው (VARP) በኖርወይ ውስጥ ባለ የመመለስ ፕሮግራም ስር ተቀባይነት እንዲያገኙ በማመልከት ወደ ትውልድ አገርዎ ለሚያደርጉት ጉዞ መተባበር ማለት ነው።

VARP ወደ ትውልድ አገርዎ የሚያደርጉትን ጉዞ የሚያመቻችልዎት በUDI እና በIOM መካከል ባለ የጋራ ትብብር ነው። በፈቃደኝነት ሲመለሱ የኖርወይ መንግስት ለመመለስ የሚወጣውን ወጪ ይሸፍናል።



ኖርወይ ውስጥ የመኖሪያ ፈቃድ የሌለው ማንኛውም ሰው በፈቃደኝነት ለመመለስ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል። የጥገኝነት ማመልከቻዎ ውድቅ ከተደረገ ከኖርወይ ለመውጣት የተወሰነ ጊዜ ይሰጥዎታል። በፍቃደኝነት ለመመለስ የሚፈልጉ ከሆነ፣ የጥገኝነት ማመልከቻዎ ውድቅ ከተደረገ በኋላ በአጭር ጊዜ ውስጥ ማመልከቻ ለIOM ማስገባት አለብዎት። ማመልከቻዎ ተቀባይነት ካገኘ IOM መምሪያ ይሰጥዎታል፣ የጉዞ ሰነዶችና የበረራ ትኬቶችን እንዲያገኙ ይረዳዎታል። በIOM በኩል ለመጓዝ በትውልድ አገርዎ ካሉ ባለስልጣናት የተሰጠ ህጋዊ ፓስፖርት ወይም ሌላ የጉዞ ሰነድ ሊኖርዎት ይገባል። ነገር ግን ሕጋዊ ፓስፖርት ወይም የጉዞ ሰነድ ከሌልዎት IOM በቅርብ ከሚገኝ ኤምባሲ/ቆንስል ሰነድ እንዲያገኙ ማመልከቻ እንዲያቀርቡ ሊያግዝዎ ይችላል። እርስዎ የሚፈልጉ ከሆነ IOM በጉዝዎ ወቅትና  ትውልድ አገርዎም ሲደርሱ ድጋፍ ሊያደርግልዎ ይችላል።

በፈቃደኝነት መመለስን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘትና የማመልከቻ ቅጹን ለመሙላት ከመጠለያ ጣቢያዎ፣ ከUDI ክልላዊ ጽ/ቤት ወይም ከIOM ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ።

**ተገዶ መመለስ፣**
ከመጨረሻው አሉታዊ መልስ በኋላ በፍቃደኝነት ወደ አገርዎ ካልተመለሱ፣ ቀነ-ገደቡ ካለፈ በኋላ ተገደው በፖሊስ ከአገሪቱ እንዲወጡ ይደረጋሉ።

ተገደው ሲመለሱ ለመመለስ የሚወጣውን ወጪ እራስዎ ይሸፍናሉ/ይከፍላሉ። የበረራ ትኬት ወጪውን እርስዎ መክፈል የማይችሉ ከሆነ የዚህን ክፍያ መንግስት ይሸፍናል፣ ነገር ግን ወጪዎቹን ሁሉ መልሰው እንዲከፍሉ ግዴታ አለብዎት። ተገደው ሲመለሱ ለሚወጣው ወጪ እርስዎ ክፍያውን ካልሸፈኑ ከዚህ በኋላ ወደ ኖርወይ እና ወደ ሌሎች የአውሮፓ አገራት የሚያስገባዎትን ቪዛ ሊከለከሉ ይችላሉ።

**ወንጀል ፈፅመው ከተገኙ፣**

የወንጀል ድርጊት ከፈፀሙ የጥገኝነት ማመልከቻዎ በጣም በፍጥነት ይታያል፣ ይህም ማለት በፍጥነት ኖርወይን ለቀው እንዲወጡ ይደረጋል ማለት ነው። አንድ ሕገወጥ ድርጊት ከፈፀሙም ከኖርወይይ እንዲወጡ ይደረጋል፣ ይህም ማለት ወደፊት ወደ ኖርወይዬም ሆነ ወይም ወደ አብዛኛዎቹ ሌሎች የአውሮፓ አገራት መግባት አይችሉም ማለት ነው።

## 6. በጥገኝነት ከለላ ዙርያ ቃለ-መጠይቅ በሚደርግልዎ ጊዜ ሊያውቁት የሚገባ አስፈላጊ ምክር፣

- የትውልድ አገርዎን ለምን ለቀው እንደወጡ እና ወደ አገርዎ ቢመለሱ የሚፈሩት ነገር ምን እንደሆነ ሙሉ በሙሉ እና በዝርዝር ይግለፁ።
- ወደ አገርዎ ቢመለሱ ሊደርስብዎ በሚችለው ነገር ላይ ያትኩሩ።
- በተቻለ መጠን በግልጽ እና በአጭሩ ይመልሱ።
- እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ከእርስዎ ጋራ ካሉ ስላሉበት ሁኔታ እና ቀደም ሲል ስለደረሰባቸው ነገር ይግለፁላቸው።
- ያልተረዱት ነገር ካለ ቃለ-መጠይቅ አድራጊውን ይጠይቁት።
- ለጥገኝነት ማመልከቻዎ ይረዱኛል ብለው ያያዙት አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች ካልዎት እነዚህን ሰነዶች ወደ ቃለ-መጠይቅ አድራጊው ይዘው ይሂዱ።
- እውነቱን ይናገሩ። እውነት ያልሆነ ነገር ከተናገሩ የጥገኝነት ጥያቄዎ ውድቅ እንዲደረግ ሊያበቃዎት ይችላል። በተጨማሪም ከኖርወይይ ለቀው እንዲወጡ ሊደረጉ ይችላሉ። ይህም ወደፊት ወደ ኖርወይ እና ወደ አብዛኛዎቹ ሌሎች የአውሮፓ አገራት እንዳይገቡ ሊያደርግዎት ይችላል።

**ሴት ጥገኝነት ጠያቂዎች፣**

ሴቶች ከወንዶች ይልቅ ለሌሎች የጥቃት/የጉዳት አይነቶች ተጋላጭ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ ጉዳይ በተለይ ለወንዶች መንገሩ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፣ እርስዎ ለመናገር የሚፈልጉ ከሆነ፣ NOAS ካሉ ሴት ሠራተኞች ጋር መነጋገር ይችላሉ። ይህን ማድረግ የሚፈልጉ ከሆነ የመረጃ ፊልሙን ከተመለከቱ በኋላ በተቻለ ፍጥነት ከ- NOAS ጋር ይማከሩበት።
ከ UDI ጋር ለሚያደርጉት ቃለ-መጠይቅ ሴት ቃለ-መጠይቅ አድራጊ እና ሴት አስተርጓሚ እንዲቀርብልዎ መጠየቅም ይችላሉ።
ይህንንም ጉዳይ በተመለከተ ከ-NOAS ጋር በሚወያዩበት ጊዜ ሊያማክሩ ይችላሉ።

**ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ከሆኑ ልጆች ጋር ነው የመጡት?**

የጥገኝነት ጥያቄውን ሁኔታ ለመመርመር የሕፃናቱ ሁኔታ በጣም አስፈላጊ ነው። UDI ሕፃኑ ጥገኝነት ለመጠየቅ የራሱ የሆኑ ምክንያቶች ያሉት ስለመሆኑ እና ሕፃኑ ያለበትን የሕይወቱን ሁኔታ እንዴት እንደሚያየው/እንደሚመለከተው ማወቅ ይፈልጋል። በጥገኝነት ቃለ-መጠይቁ ወቅት ስለዚህ ሁኔታ ለUDI መናገር አስፈላጊ ነው።

UDI እድሜያቸው ከሰባት ዓመት በላይ የሆኑ ልጆችን ቃለ-መጠይቅ ያደርጋል። ልጁ/ልጅት በራሱ /በራሷ ቋንቋ እና አገላለጽ የደረሰበትን/የደረሰባትን ነገር የመግለጽ እድል ማግኘቱ አስፈላጊ ነው። አንዳንድ ጊዜ ሕፃናት ከአዋቂዎች የበለጠ አስከፊ ችግሮች ሊደርሱባቸው ይችላል። ልጆቹ እራሳቸው ቃለ-መጠይቅ እንዲደረግላቸው እስካልፈለጉ ድረስ UDI ልጆችን ቃለ-መጠይቅ አያቀርብላቸውም።

## 7. እንደጥገኝነት እና ከለላ ጠያቂነትዎ ሊኖርዎት የሚችለው መብትና ግዴታ፣

**ስለ ማንነትዎ ለማሳወቅ ትብብር የማድረግ ግዴታ አለብዎት**

እርሶ ማን እንደሆኑ የኖርወይ መንግሥት ማወቁ አስፈላጊ ነው። ለዚህም ነው የእርስዎን ማንነት የሚያረጋግጡ ሰነዶችን ማቅረብ አስፈላጊ የሚሆነው። በትውልድ አገርዎ ባሉ ባለስልጣናት ክትትል የተፈፀመብዎት ከሆነ የኖርወይይ ባለስልጣናት የመታወቂያ ሰነዶችን እንዲያገኙ ከመንግሥትዎ ጋር ግንኙነት እንዲያደርጉ አያስገድድዎትም።

የኖርወይይ ባለስልጣናት ስለማንነትዎ ጥርጣሬ ካደረባቸው፣ የሚከተሉት አሳሳቢ ጉዳዮች ሊያጋጥምዎት ይችላል፡-

- ያለመታመን
- የመኖሪያ ፈቃድ የማግኘት እድልዎ የመጥበብ፣
- ሊሰጥዎ የሚችሉ መብቶችን የማጣት፣
- የተገደበ የመኖሪያ ፈቃድ ማግኘት

**ትክክለኛ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለብዎት።**

እንደ ጥገኝነት ጠያቂ ለምን ጥገኝነትና ከለላ እንደሚጠይቁ ማብራራት ይኖርብዎታል። ስለሆነም በተቻለዎት መጠን ለመተባበር እና አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ለማቅረብ የሚችሉትን ሁሉ ማድረግ ይኖርብዎታል።
የጥገኝነት ከለላ ለማግኘት ከማመልከትዎ በፊት በወሬ ከሌሎች ሰዎች የሰሟቸውን ነገሮች ሁሉ ወደ ጎን በመተው ለኖርወይ ባለስልጣናት ለጥገኝነት ጥያቄዎ ትክክለኛውን የእርስዎን ማንነት የሚመለከት መረጃ መስጠት እና መግለጽም አስፈላጊ ነው። ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ መስጠት ያስቀጣል። ከሃገር እስከማባረርም ሊያደርስ ይችላል።

**የጥገኝነት ከለላ መልስ እየጠየቁ ባሉበት ወቅት የመስራት መብት ሊኖርዎት ይችላል**

የጥገኝነት ማመልከቻዎ እየታየ ባለበት ወቅት ማንነትዎን በተመለከተ በቂ መረጃ ማቅረብ ከቻሉ እና በዳብሊን ስምምነት መሠረት ጉዳይዎት እየታየ ካልሆነ የሥራ ፈቃድ ሊያገኙ ይችላሉ። የሥራ ፈቃዱ እስከ 6 ወራት ለሚሆን ጊዜ የሚያገለግል ሲሆን መታደስም ይችላል።

**ሕክምና የማግኘት መብት አለዎት።**

የጥገኝነት ማመልከቻዎ እየታየ ባለበት ወቅት የሚያስፈልግዎትን ሕክምና የማግኘት መብት ይኖርዎታል። እድሜያቸው ከ12 ዓመት በታች ለሆኑ ልጆች ህክምና የሚሰጠው በነፃ ነው። በኖርወይይ ውስጥ ያለ ማንኛውም ሰው አብዛኛውን ጊዜ ለሚደረግለት ሕክምና የግል ድርሻ ክፍያ መክፈል አለበት። የሥነ-አእምሮ ሃኪም ድጋፍ የሚፈልጉ ከሆነ ወጪዎችን UDI እንዲሸፍን ማመልከት ይችላሉ። ለተጨማሪ መረጃ የመጠለያ ማዕከሉን ሠራተኞች ያነጋግሩ። አደገኛ የጤና ችግሮች ካለብዎ ለUDI የማሳወቅ ግዴታ አለበዎት።

**የጥገኝነት ማመልከቻዎትን ማንሳት ይችላሉ፣**

የጥገኝነት ማመልከቻዎ መታየቱ እንዲያቆም በማናቸውም ጊዜ ማድረግ ይችላሉ። ከዚህ በኋላም ወደ ትውልድ አገርዎ ለመመለስ ለIOM ማመልከቻ ማቅረብ ይቻላል።

## 8. ምስጢር የመጠበቅ ግዴታ፣

ፖሊስ፣ UDI ፣ UNE ፣ አስተርጓሚ፣ ጠበቃ፣ የጤና ባለሞያ እና NOAS ሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው። ይህም ማለት የጥገኝነት ማመልከቻዎትን በተመለከተ ለትውልድ አገርዎ መንግሥት መረጃ መስጠት አይችሉም ማለት ነው። በእርስዎ የጥገኝነት ማመልከቻ ላይ ለማይሳተፉ ሰዎች እርስዎ ስለተናገሯቸው ነገሮች ምንም ነገር መንገር አይችሉም። ሚስጥር የመጠበቅ ግዴታን አለመወጣት ያስቀጣል ስለሆነም ጥበቃ ስለፈለጉበት ምክንያት በዝርዝር መግለጽን መፍራት አይኖርብዎትም ማለት ነው።

# አድራሻዎች

## የኢሚግሬሽን ፖሊስ ክፍል (POLITIETS UTLENDINGSENHET)

ፖሊስ አዲስ የገቡ ጥገኝነት ጠያቂዎችን ይመዘግባል።
አንድ ጊዜ የጥገኝነት ማመልከቻቸው ኣሉታዊ መልስ ካገኘ በኋላ በፈቃዳቸው ከኖርወይይ ያልወጡ ጥገኝነት ጠያቂዎችን ያስወጣል።

**የፖስታ አድራሻ:** Postboks 8102 Dep., NO-0032 Oslo, Norway
**የመጠየቂያ አድራሻ:** Christian Krohgs gate 32, Oslo
ስልክ.: +47 22 34 24 00, ፋክስ: +47 22 34 24 80
ኢ-ሜይል: pu@politiet.no

## የኖርወይይ የኢሚግሬሽን ጉዳይ ዳይሮክቶሬት /UDI/

ግዴታዎቹ የጥገኝነት ማመልከቻዎችን፣ ቪዛ እና የዜግነት ጉዳዮችን ማየትን እና ቤተሰቦችን መልሶ ማገናኘትን የሚያካትት መንግስታዊ ተቋም ነው። ከዚህ በተጨማሪ UDI ለቅበላ ማዕከላቱ ኃላፊነት አለበት።

**የፖስታ አድራሻ:** Postboks 8108 Dep., NO-0032 Oslo, Norway
**የመጠየቂያ አድራሻ:** Hausmannsgt. 21, 0182 Oslo
ስልክ.: +47 23 35 15 00, ፋክስ: +47 23 35 15 01
ድረ-ገፅ: www.udi.no, ኢ-ሜይል: ots@udi.no

## ዓለም አቀፍ የስደተኞች ድርጅት /IOM/

በፈቃደኝነት ድጋፍ አግኝቶ መመለስን በተመለከተ የቀረበ መረጃ

**የፖስታ አድራሻ:** Postboks 8927 Youngstorget, NO-0028 Oslo, Norway
**የመጠየቂያ አድራሻ:** Storgata 10a, ሁለተኛ ፎቅ, Oslo
ስልክ.: +47 23 10 53 20, ፋክስ: +47 23 10 53 21
ኢ-ሜይል: osloreturn@iom.int

የስራ ሰዓታት: በስራ ቀናት: 10:00 – 15:00, ቅዳሜ እና እሁድ: ዝግ ነው

**የኖርወይ የስደተኞች ይግባይ ቦርድ (UTLENDINGSNEMNDA – UNE)፣**
የተወሰኑ ተቀባይነትን ያጡ ማመልከቻዎች ጋር በተያያዙ የሚቀርቡ ይግባኞችን የሚያይ ከፊል የዳኝነት አስተዳደር አካል ነው።

**የፖስታ አድራሻ:** Postboks 8165 Dep., NO-0034 Oslo, Norway
**የመጠየቂያ አድራሻ:** Stenersgt. 1B/C, 0050 Oslo
ስልክ.: +47 21 08 50 00, ፋክስ: +47 21 08 50 01
ድረ ገፅ: www.une.no, ኢ-ሜይል: postmottak@une.no

**የኖርወይ ቀይ መስቀል (NORGES RØDE KORS)**
በቤተሰብ አባላት መካከል በጦርነት፣ በግጭት ወይም በአደጋ ምክንያት መለያየት ሲከሰት መልሰው እንዲገናኙ ግንኙነቶችን የሚያመቻች እና አገልግሎቶችን የሚሰጥ ድርጅት ነው።
ቀይ መስቀል ለUDI ወይም ለሌሎች እርስዎን በተመለከተ መረጃ አይሰጥም። የሚሰጠው አገልግሎትም ነፃ ነው።

**የፖስታ አድራሻ:** Postboks 1 Grønland, NO-0133 Oslo, Norway
**የመጠየቂያ አድራሻ:** Hausmannsgt. 7, 0186 Oslo
ስልክ.: +47 22 05 40 00
ድረ ገፅ: www.rodekors.no, ኢ-ሜይል: tracing@redcross.no

**NOAS** መንግሥታዊ ያልሆነ የሰብአዊ መብት ድርጅት ሲሆን፣ሥራውም መረጃንና የህግ እርዳታን ጥገኝነትና ከለላን ለሚጠይቁ ሰዎች መስጠት ነው:: እንዲረዳ ሆኖ የተቋቋመ ድርጅት ነው::

ይህ ጥራዝ ለእርስዎ በኖርወይ ውስጥ ጥገኝነትንና ከለላን ለሚፈልጉ ሰው ጠቃሚ መረጃዎችን እንዲያካትት ተደርጎ የተዘጋጀ ነው::


**ኖርወጂያዊ ድርጅት ለጥገኝነት ጠያቂዎች (NOAS)**
**የጉብኙት አድራሻ:** Torggata 22, Oslo, Norway
**የፖስታ አድራሻ:** P.O.Box 8893 Youngstorget, NO-0028 Oslo, Norway
ስልክ: +47 22 36 56 60, ፋክስ: +47 22 36 56 61
ድህረ ገጽ: www.noas.org, ኢ-ሜይል: noas@noas.org